የመ/ቁ 268417

ጥቅምት 20 ቀን 2013 ዓ.ም

ልደታ ምድብ 14ኛ ፍ/ብሔር ችሎት

ዳኛ፡- ግዛው ኃ/ሚካኤል

ከሳሾች፡- 1. ወ/ሮ የሸዋዘውድ ሙሴ

2. አቶ ያሬድ በለጠ

3. ወ/ሮ ሐራን በለጠ

4. ወ/ሮ ትርሲት በለጠ

ተከሳሾች፡- 1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

2. የአዲስ አበባ ከተማ ፕላን ኮሚሽን

3. የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነው፡፡ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጠ፡፡

ፍ ር ድ

ከሳሽ ጥቅምት 20 ቀን 2011 ዓ/ም አሻሽለው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ አንደኛ ከሳሽ እና ሁለተኛ እስከ 4ተኛ ለተጠቀስነው ከሳሾች አባት እና አውራሽ የሆኑት ኮሎኔል በለጠ ረዴ በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17 ውስጥ በሚገኘው የቦታ ስፋት 2084 በሆነ መሬት ላይ በ280 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ የምድር ውስጥ እና ከምድር በላይ በሸክላ እና በውድ የመጨረሻ/ፉኒሺንግ/ ስራዎች የተሰራ ቤት ነበረን ። አንደኛ ተከሳሽ ድንገተኛ በሆነ ሁኔታ በ1996 ዓ.ም መሬቱን ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን 2ኛ ደረጃ ማስፋፊያና በካዛንችስ የአካባቢ ልማት ዕቅድ ስለምፈልገው እንድትለቁ የሚል ትእዛዝ ሰጠን ። እኛም መሬቱ ለአካባቢ ልማት ዕቅድ ከተያዘ እኛው ማልማት ስለምንችል እንድናለማው ይፈቀድልን ብንልም ሰሚ ልናገኝ አልቻልንም ። ይልቁንም ዋናው ቤት እና አጥሩ እንዲሁም ምድረ ግቢው በምርጥ የግንባታ እቃዎች የለማ በመሆኑ በወቅቱ ዋጋ እንኳ ቤቱ በትንሹ ብር 5000000 (አምስት ሚሊዩን) የሚያወጣ ሆኖ ሳለ 1ኛ ተለሳሽ የቤቱ ግምት 361529.16 ነው በማለት ይህንኑ ሰርቪስ ቤት እንኳ በአግባቡ የማይሰራ ገንዘብ ሰጥቶን በወቅቱ እንደ መብራት፣ ውሃ ፣ መንገድ፣ስልክ ወዘተ የሌለበት፣ከምንኖርበት ቦታ 15 ኪ.ሜ የራቀ፣በዝምድና በጉርብትና በእድር ወዘተ አብረን ከኖርነው ማህበረሰብ በመነጠል በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ውስጥ የሚገኝ 500 ካ. ሜ ስፋት ያለው ቦታ ሰጠን ። ይህ ሁሉ ጉዳት ታይቶ ካሳ እንዲሻሻልልን ፣ በአካባቢው ካለው ኪስ ቦታ እንዲሰጠን ቤት ለመስሪያ የሚበቃ ጊዜ እንዲሰጠን በየደረጃው ብናመለክትም ውጤት አልባ ሆኖ ካሳ ነው ተብሎ የተሰጠንን በመያዝ ወደ አዲሱ ምድረ በዳ ተጓዝን ።ነገር ግን ለልማት በሚል የተወሰደብን መሬት ኢንቨስተር ለተባለ ግለሰብ ተሰጥቶ እስከ አሁን ድረስ ግንባታው በጅምር ቀርቷል ። በተሰጠን 500 ካ.ሜ ላይ ግራውንድ + 1 የሆነ ቤት ገንብተን በበጋ ከአቧራው በክረምት ከጭቃው ጋር እየታገልን እየኖርን ሳለ 3ኛ

ተከሳሽ ወደ መኖርያ ስፍራችን በመምጣት 2ኛ ተከሳሽ ባወጣው አዲስ የመንገድ ፕላን መሰረት በቤቱ ጎን የሚገነባ 20 ሜትር ስፋት ላለው መንገድ መስሪያ ቦታ ስላልበቃን ወደ ቤታችሁ ከ2.6 እስከ 3 ሜትር መጠጋት አስፈልጎናልና ግምቱን ከ1ኛ ተከሳሽ ወስዳችሁ አጥራችውን አፍርሱ የሚል የቃል ትእዛዝ ሰጠን ።

ከሳሾች ወደ 2ኛ ተከሳሽ በመሄድ ቦታ የተሰጠን ለመንገድ ግንባታ ከታቀደው 20 ሜትር ገብቶ ነው ። ካርታችንም ይህንኑ ያረጋግጣል ይህ የመንገድ መስሪያ ቦታ እያለ ወደ ከሳሾች ቤት በሚገባ ሁኔታ እንዴት የፕላን ማሻሻያ ተሰራ፣ አሁን ተሻሽሎ ተሰራ ባላችሁት የመንገድ ፕላን መሰረት ወደ ቤታችን ብትጠጉ የቤት ፍሳሽ ማስተላለፊያ ቱቦ መፍረሱ የግድ ስለሚሆን የቤቱ መሰረትም ስለሚፈርስ ቤታችን ዳግም በመንገድ ስራ ምክንያት ሊፈርስ ነው ብለን ስንጠይቅ 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ከፈቀዱ ቤቱን በማይነካ ሁኔታ ሌላ ፕላን ማውጣት እንችላለን ወደእናንተ ይዞታ የሚገባ የመንገድ ፕላን የሰራነው በአካባቢው በመገንባት ላይ ካለው የ40/60 ቤቶች ውስጥ 3ቱ ብሎኮች በቅየሳ ችግር ምክንያት ወደ መንገድ መስሪያው ቦታ ገብተው በመገንባታቸው ነው የሚል የቃል መልስ ሰጠን ። ሦስቱም ተከሳሾች ስለሁኔታው በፅሁፍ ሊያሳውቁን አልፈቀዱም ። በህጉ መሰረት ማፈግፈግ የሚገባው ለህዝብ ጎዳና በተከለለ መሬት ላይ የ40/60 ሕንፃዎቹን የገነባው አካል ነው እንጂ ትክለኛውን ፕላን ጠብቀን በተሰጠን ቦታ ላይ ቤት የሰራነው ከሳሾች ልንሆን አይገባም ።

ከላይ የቀረበው ቢታለፍ ተከሳሾች ከዜጎች ከመኖሪያ ቦታቸው ያለአግባቡ ያለመፈናቀል ንብረት የማፍራት እና በንብረት የመጠቀም ወዘተ መብት ይልቅ 1ኛ ተከሳሽ በሕንፃ ግንባታ የሰራው ስህተት እንዳይታወቅበት እና ይህንን ስህተት ለማረም የሚያስፈልገውን ወጪ ላለማውጣት በመፈለጉ እንጂ ከከሳሾች ቤት ቀጥሎ ከ40/60 ቤቶቹ ፊት ላፊት ምንም ግንባታ ያልሰፈረበት በአብዛኛው ቦዶ የሆነ ቦታ ስላለ የመንገዱን ፕላን እስከ ከሳሾች ቤት ድረስ

በቀድሞው ፕላን መሰረት በመስራት 40/60 ሕንፃዎቹ ጋር ደግሞ ወደ ባዶ ቦታው ገባ በማለት መስራት ሲቻል የከሳሾች ንብረት በሚፈርስበት ሁኔታ ለመፈጸም መታቀዱን አግባብ አይደለም ። በሌላ በኩል ለመንገድ ስራ የሚያስፈልገው ቦታ ከአንድ ወገን ብቻ ሳይሆን ከመንገዱ ግራና ቀኝ አዋሳኞች በእኩል ሁኔታ በመቀነስ አንድ ወገን ብቻ ሳይጎዳ መፈጸም ሲቻል ይህ አለመደረጉ አድሎነት ስለሆነ አግባብ አይደለም ።አንደኛ ተከሳሽ የሚፈርሰው አጥርና ንብረት በተገቢው ሁኔታ እንዲገመት ሳያደረግ እና ካሳውን ሳይከፍል ንብረት ላፍርስ ማለቱ የሕግ አግባብ የለውም ።

በመሆኑም 1ኛ ተከሳሽ የከሳሾችን አጥር እና ቤት በማይነካ ሁኔታ መንገዱን እንዲያስገነባ፣2ኛ ተከሳሽ አለአግባብ ያዘጋጀው የመንገድ ፕላን እንዲሰረዝ እና 3ኛ ተከሳሽ ይዞታችንን በሚነካ መልኩ መንገዱን እንዳይገነባ እንዲወሰንልን፣ተከሳሾች የፈጠሩትም የሁከት ተግባር እንዲወገድልን በማለት ጠይቀው ክክሳቸው ጋር የሰነድ እና የሰው ምስክር ዝርዝር አቅረበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል።

ከሳሾች ያቀረቡት የክስ አቤቱታ ከፍ/ቤቱ መጥሪያ ጋር ለተከሳሾች ደርሷቸው ቀርበው መልስ ሰጥቷል። 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጽፈው በቀረቡት የመከላከያ መልስ የመ/ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ መልስ አቅረበዋል።በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ፍ/ቤቱ ግንቦት 08 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ብይን ሰጥቶበታል። 1ኛ ተከሳሽ ህዳር 7 ቀን 2011 ዓ.ም ባቀረቡት አማራጭ መልስ ከሳሾች ባቀረቡት ክስ የመንገድ ግንባታዉ ከታቀደዉ 20 ሜትር ገብቶ እንደሆነና የቀደመዉ ፕላን የቤታቸዉን ፕላን እንደማይነካና የ40/60 የቤቶች ልማት ወደ መንገድ መስሪያዉ ገባ በማለቱና በቅየሳ ችግር ምክንያት እንደሆነ አድርገዉ ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢ ያልሆነና በበቂ ማስረጃ ያልተደገፈ አቤቱታ ሲሆን የቀደመዉ ፕላን የከሳሾችን

አጥሩን እንደማይነካ ፕላኑን ሳያቀርቡ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የቀረበዉን የክስ አቤቱታ ዉድቅ ሊያደርገዉ ይገባል፡

ከሳሾች የአያት መሪ ሳይት 4 የመንገድ ፕሮጀክት የአጥር ይዞታቸዉን የሚሰራዉ መንገድ የሚነካዉ መሆኑ የታመነ ነዉ ፡፡በመሆኑም የተሰጠን ካርታ እና የሰራሁት በትክክለኛ የመንገድ ጥናትን በማይነካ ነዉ ይበሉ እንጂ ቤቱን ሲሰሩ በባለሞያ ባግባቡ ሳያስጠኑና የተሰጣቸዉ የቾካል ኮርድኔትን በመሃንዲሳቸዉ እንዲረጋገጥ ባለማድረጋቸዉ ምክንያት የተፈጠረ እንጂ እንደ ከሳሾች የክስ አቀራረብ የ40/60 ኮንዶምንየም ፕላኑ በመሻሻሉ ባለመሆኑ የቀረቡት ክርክር ተገቢነት የሌለዉ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከሳሾች ተከሳሽ የሚፈርሰዉን አጥር እና ንብረት በተገቢዉ ሁኔታ እንዲገመት ሳያደርግ ላፍርስ ማለቱ አግባብ አይደለም ያሉትን በተመለከተ ባለሞያዎች ወደ ከሳሾች ቤት በመሄድ አስፈላጊ ግምቶች እንዲሰራላቸዉ ካርታቸዉን እንዲያቀርቡ ጠይቀዋቸዉ አልሰጥም ብለዉ ስራዉን ለማደናቀፍና እንዲጉተት እያደረጉ ሲሆን ለዚህ ፍ/ቤት ደግሞ የተሰራ ካሳ የለም በማለት እርስ በርሱ የሚጣረስ አቤቱታ ተገቢነት የሌለዉ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ ሊያደርግ ይገባል ፡፡ ከሳሾች ለመንገዱ ስራ የሚያስፈልገዉ ቦታ ከአንድ ወገን ብቻ ሳይሆን ከመንገዱ ግራና ቀኝ አዋሳኞች በእኩል ሁኔታ በመቀነስ አንድ ወገን ብቻ ሳይጎዳ መፈፀም ሲቻል ይህ አለመደረጉ አድሎነት በመሆኑ አግባብ አይደለም በማለት ያቀረቡት ክስ በመጀመርያ አጠቃላይ የመንገዱን የፕላን ቅየሳ ተግባር ባግባቡ ሳይረዱና በበቂ ማስረጃ ሳያረጋግጡ ያቀረቡት ክስ ነዉ ፡፡የመንገዱ ፕላን ሲወጣ አንድ ወገንን ለመጉደት ታስቦ የወጣ ሳይሆን የአካባቢዉን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ለማሳደግና ከሳሾችን ጨምሮ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ እንጂ እንደ ከሳሾች አቀራረብ የመንገዱ አንድ ወገን ለመጉዳት ታሳቢ አላደረገም የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን በቀን 11/11/2010 በቁጥር የ/መ/ቤ/የመ/ግ/አ/

ዳ/009/11 በሆነ ደብዳቤ እንደገለፀዉ መንገዱ የሚነካባቸዉን ዝርዘር መብራሪያ ሲሰጥ የመንገዱ አጠቃላይ ቅየሳ በሀሉም አቅጣጫ የግራና ቀኝ የሚነካ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ከሳሾች ፕላኑ ከአንድ ወገን ነዉ የተሰራዉ ሲሉ የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢ ያለመሆኑን ያስገነዝባል ። በተከለለ ቦታ ላይ የ40/60 የመኖርያ ቤቶች ህንፃዎችን ገንብቶዋል እኛ ደግሞ ፕላን ጠብቀን ሰርተናል በፍ/ብ/ህግ ቁ 1452/1/ መሰረት የማፈግፈግ ግዴታ የለብንም ሲሉ አቤቱታቸዉን አቅርበዋል ።ይሁንና የተሳሳተ ፕላን ነዉ በማለት ከሳሾች አቤቱታ ያቅርቡ እንጂ ለዚሁ አባባላቸዉ የሚያግዛቸዉን ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ ክስ ማቅረባቸዉ ተገቢነት የሌለዉ ነዉ በሌላ በኩል ደግሞ የፍ/ህ/ቁጥር 1459/1/ መሰረት ለህዝብ አገልግሎት የተመደበዉን ንብረት አጠባበቅን የሚጎዳ ማናቸዉም ስራ እንዲፈርስ የአስተዳደር ክፍል በማናቸዉም ጊዜ ለማዘዝ ይችላል ሲል የገለፀ በመሆኑ የአቀረቡት አቤቱታ ተገቢነት የሌለዉ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ክሱን ዉድቅ ሊያደርግ ይገባል በማለት ከመልሳቸው ጋር የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘው አቅርበዋል።

2ኛ ተከሳሽ ባቀረቡት አማራጭ መልስ ከሳሾች ባቀረቡት ማስረጃ መሰረት የመዋቅራዊ ፕላኑ 20 ሜትር ዋና መንገድ የከሳሾችን የመኖሪያ ቤት ይዞታ የሚነካ አይደለም።ጉዳዩን ለማጣራት በሂደት ላይ እያለን ክሱ መቅረብም ተገቢነት የለውም። ከሳሾችን ለማጉዳት በ2ኛ ተከሳሽ ሆን ተብሎ የተደረገ ነገር የለም።1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ከፊቀዱ ቤቱን በማይነካ ሁኔታ ሌላ ፕላን ማውጣት እንችላለን በማለት 2ኛ ተከሳሽ ለከሳሽ የገባው ቃል የለም፣ሌላ የዋና መንገድ ፕላን የማውጣት ስልጣንም ለ2ኛ ተከሳሽ በህግም አልተሰጠም።የ40/60 ቤቶች ውስጥ ሶስቱ ብሎኮች በቅያሳ ችግር ምክንያት ወደ መንገድ መስሪያው ቦታ ገብተው በመገንባታቸው ነው የሚል የቃል መልስም ለከሳሾች በ2ኛ ተከሳሽ የተሰጠ ባለመሆኑ የከሳሽ ክስ ውድቅ እንዲሆን በማለት ጠይቋል።ከመልሳቸው ጋር የሰነድ እና የሰው ምስክር ዝርዝር አቅረበዋል።

3ኛ ተከሳሽ ህዳር 17 ቀን 2011 ዓ.ም በአማራጭ በሰጡት መልስ ከሳሾች በክስ ዝርዝራቸው የጠቀሷቸው የመፈናቀል ሁኔታ በ3ኛ ተከሳሽ ምክኒያት የተፈጠረ እንዳልሆነ ተከሳሽም የማያውቀውና የማይመለከተው እንዲሁም ከቀረበው ክስ ጋር የማይገናኝ ነው፡፡3ኛ ተከሳሽ ለከሳሾች የሰጠ የቃል ትዕዛዝ የለም፡፡በአዋጅ ቁጥር 455/1997 አንቀጽ 3 መሠረት መሬትን ካሳ እንዲከፈል በማድረግ የማስለቀቅ ስልጣን የተሰጠው ለወረዳና ለከተማ አስተዳደር ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር አስፈፃሚ ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 17 እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬት ላይ የሚገኝ ንብረት ግምት የሚሰራው የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ጽ/ቤት እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 7/1990 አንቀጽ 8 ባለስልጣኑ በሚጠቀምበት መሬት ላይ ለሰፈሩ ንብረቶች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተገቢውን ካሳ መክፈል እንዳለበት አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ አዋጆችና ደንብ የምንረዳው 3ኛ ተከሳሽ ለሚያሰራቸው መንገዶች ክ/ከተማው የካሳ ክፍያ የሚገባቸውን ግለሰቦች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለይቶ እና የክፍያ መጠኑን ገልጾ ሲያቀርብለት ብቻ ተገቢውን ካሳ ከመክፈል ውጭ ቦታ የማስለቀቅም ሆነ የካሳ ግምት የመስራት ስልጣን የሌለው በመሆኑ ከሳሾችን በቀጥታ ቤታቸው ድረስ በመሄድ ልቀቁ የሚልበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም ከሳሾች ያቀረቡት አቤቱታ ሀሰት እና እውነታነት የሌለው ስለሆነ 3ኛ ተከሳሽ የፈጠረው የሁከት ተግባር የለም፡፡

በአካባቢያችን በተሰራው 40/60 ኮንዶሚኒየም ምክንያት ቀድሞ የነበረው ፕላን በመሻሻሉ የመንገዱን ግራና ቀኝ አዋሳኞችን በእኩል ሁኔታ በመቀነስ አንድ ወገን ብቻ ሳይጎዳ መስራት ሲቻል ይህን ባለማድረግ በአንድ ጎን ብቻ በማስፈረስ አድሎአዊነት መፍጠሩ አግባብ አይደለም በማለት የቀረበው አቤቱታ የመንገዱ ፕላን ቀድሞ በነበረው መሠረት እየተሰራ ባለበት ሁኔታ ፕላን ተሻሽሎ ተሰርቷል በማለት የቀረበው ክስ ሀሰት ሲሆን የተሻሻለ ፕላንም የለንም፡፡ የመንገድ ፕሮጀክቱ አማካሪ መሃንዲስ ኮር ኮንሰልቲንግ ኢንጂነርስ ኃላ/የተ/የግ/ማሕበር በቁጥር

CORE/AM/007/18 በቀን JunE 13/2018 በተፃፈ ደብዳቤ በመንገዱ ወሰን ውስጥ በግራ እና በቀኝ መንገድ ወሰን ውስጥ የሚገኙ ግንባታዎች፣ የመብራት፣ የውሃ እና የቴሌ መስመሮችን እንዲነሱ የሚያሳይ መረጃ አጣርቶ የላከልን በመሆኑ የወሰን ማስከበር ስራው በዚህ መረጃ መሠረት እንዲፈፀምልን ለሚመለከተው አካል ከማሳወቅ በቀር ከሳሾች እንደሚሉት አንዱን አካል በመጥቀም ሌላውን አካል ለመጉዳት በማሰብ የተሰራ ስራም ሆነ ዲዛይን የለም።

20 ሜትር ስፋት ያለው የመንገድ አካል በመገንባቱ ምክንያት ሌላውን አካል ለማዳን በማሰብ ቤታችን ከ2.6 እስከ 3 ሜትር ድረስ እንዲፈርስ መደረጉ አግባብነት የለውም፣ ቤታችንን የሰራነው መንግስት በሰጠን ካርታ መሠረት ነው በማለት የካርታ ቁጥር ቦሌ10-1/39/7/9/ሃ-443/18711/01 የቦታ ስፋቱ 500m^2 መሆኑን የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ አቅርበዋል። በቀረበው የሰነድ ማስረጃ መሠረት መሬት ላይ የሚገኘው የከሳሾች የግል ይዞታ እና በካርታው የሚታየው የቸካል ኮርድኔት ተመሳሳይነት ያለው አይደለም። የካርታውን ኮርድኔት በመውሰድ ፕላኑ ሲታይ የመንገዱ ፕላን ይዞታውን እንደማይነካው ያሳያል። ነገር ግን በከሳሾች የተገነባው ግንባታ መሬት በመውረድ ሲታይ የግንባታው ኮርድኔት ከቀረበው ካርታ በተለየ መልኩ በመሆኑ የከሳሾች ግንባታ በሚገነባው የመንገድ አካል ላይ ወጥቶ የሚገኝ መሆኑን ባለሞያዎች ማረጋገጥ ችለዋል። በማስረጃነት የቀረበው የይዞታ ካርታ Actual (አሁን) መሬት ላይ የሚታየውን ግንባታ አያስረዳም። ይህም ከሳሾች በራሳቸው ስህተት በካርታ የተሰጣቸው ኮርድኔት በመሳት የገነቡት ግንባታ የመንገድ ፕላኑ ላይ መውጣቱ በራሳቸው ችግር የተፈጠረ ስህተት ሆኖ ሳለ ሌላውን ለመጥቀም በማሰብ የመንገድ ፕላን ለውጥ ተደርጎ አድሎ እና ሀሰት ተፈጥሮብናል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ እውነትነት የለውም።የጉዳት ካሳ ለከሳሾች ከመከፈሉ በፊት 3ኛ ተከሳሽ መንገዱን እንዳይገነባ /እንዳያስገነባ/ ይታዘዝልን በማለት ለፍ/ቤቱ ለተጠየቀው ዳኝነት በከተማዋ ውስጥ የሚገነቡ መንገዶች አገልግሎታቸው ለሕዝብ ጥቅም ከመሆኑ አንፃር ብቻም ሳይሆን ምንም አይነት ጉዳት በከሳሾች ላይ ሳይደርስ ጉዳት እንደደረሰ

በማስመሰል ለቀረበ አቤቱታ ፍ/ቤቱ እየተሰራ ያለን መንገድ እንዳይገነባ ወይም ስራው እንዲቆም ትእዛዝ የሚሰጥበት የሕግ መሠረት የሌለ ሲሆን 3ኛ ተከሳሽ እያስገነባ ባለው የመንገድ ስራ ላይ በመንገድ ፕላኑ መሠረት በመንገድ ወሰን ክልል ውስጥ ለገባ ይዞታ በአዋጅ ቁጥር 455/96 መሠረት የካሳ ግምት ተሰርቶ ሲቀርብልን የመክፈል ግዴታ ያለብን መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም የከሳሾች ይዞታ በመንገድ ፕላኑ ላይ በመንገድ ወሰን ክልል ላይ የሚገኙ ከሆነ የካሳ ግምት ተሰርቶ እንዲቀርብላቸው የሚመለከተውን አካል መጠየቅ እና ለግምት ስራውም መተባበር ሲገባቸው 3ኛ ተከሳሽ እያስገነባ ያለው የመንገድ ስራ እንዳይገነባ /እንዲቆም/ የፍ/ቤት ትእዛዝ መጠየቃቸው የሕግ መሠረት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር ፍ/ቤቱ ይህን ትእዛዝ ቢሰጥ በመንግስት ሐብትና ንብረት ላይ ከሚደርሰው ጉዳት በላይም የሕዝብ መንገላታት እና የመልካም አስተዳዳር ችግር የሚፈጥር በመሆኑ ፍ/ቤቱ ከሳሾች ያቀረቡትን ጥያቄ በመቀበል ትእዛዝ ከመስጠት ይልቅ የሚገባቸውን የካሳ ግምት አሰርተው የካሳ ክፍያቸውን ይጠይቁ የሚል ትእዛዝ በመስጠት ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ እንዲያደርግልን በማለት ከመልሳቸው ጋር የሰነድ ማስረጃ እና የሰው ምስክር ዝርዝር አቅረበዋል፡፡
ክስ በተሰማበት ቀን ግራ ቀኙ በፅሁፍ ያቀረቡትን መከራከሪያ በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር እና ማስረጃ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን **ፍ/ቤቱም ተከሳሾች በከሳሾች ላይ የፈጠሩት የሁከት ተግባር አለ ወይ ?** የሚለውን ጭብጥ በዋነኝነት በመያዝ ሌሎች ነጥቦች በተያዙት ጭብጥ ስር ምላሽ የሚያገኙ ሆነው መዝገቡን አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ፍ/ቤቱ መዝገቡን እንደመረመረው በፍ/ብሄር ህግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ላይ እንደተመለከተዉ በእጁ አድርጎ በእዉነት በሚያዝበት ይዞታዉ ላይ ሁከት የተነሳበት ሰዉ የተነሳዉ ሁከት በፍርድ ሀይል እንዲወገድለት ለመጠየቅ የሚችል ሲሆን ይዞታዉን በህግ

አግባብ ያገኘዉ መሆኑንም በማረጋገጥ ክስ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑም የፍ/ብ/ህ/ቁ 1140 እና 1146 ይደነግጋሉ ።

በዚህ መዝገብ የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት ከሳሾች ባቀረቡት ክስ በ1ኛ ተከሳሽ አሰሪነት በ2ኛ ተከሳሽ ፕላን ሰርነት እና በ3ኛ ተከሳሽ መንገድ ሰርነት የሚገነባው የመንገድ ልማት ይዞታችንን በሚነካ መልኩ ፕላኑ በመሠራቱ እና ለማስራትም ይዞታችንን በሚነካ ሁኔታ እንቅስቃሴ መደረጉ የሁከት ተግባር በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ 1ኛ ተከሳሽ የከሳሾችን አጥር እና ቤት በማይነካ ሁኔታ መንገዱን እንዲያስገነባ፣2ኛ ተከሳሽ አለአግባብ ያዘጋጀው የመንገድ ፕላን እንዲሰረዝ እና 3ኛ ተከሳሽ ይዞታችንን በሚነካ መልኩ መንገዱን እንዳይገነባ እንዲወሰንልን በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተከሳሾች በበኩላቸው ለመሰራት እየተዘጋጀ ያለው የመንገድ ግንባታ ከሳሾች ይዞታ የማይነካ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ጠይቋል።

ፍ/ቤቱ በግራ ቀኙ ያቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎችን የተመለከተ ሲሆን በግራ ቀኙ የቀረቡት ሰነዶች ግራ ቀኙ በተገኙበት የተሰጡ ባለመሆናቸው እና መንገዱ የከሳሽን ይዞታ የሚነካ መሆን አለመሆኑን በገለልተኛ አካል እቦታው ድርስ በመሄድ እንዲጣራ ትዕዛዝ በመስጠት አጣርቷል።ጉዳዩ በሰው ምስክር የሚጣራ ባለመሆኑ በዝርዝር የቀረቡትን የሰው ምስክሮችን ሳይሰማቸው አልፏቸዋል።

ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በደብዳቤ ቁጥር አከ8/20/11-100 በ13/11/2012 በሰጠው ምላሽ ለከሳሾች ይዞታ የተሰጣቸው የመንገዱ ፕላን ከጸደቀ በኃላ መሆኑን፣የመንገዱ ፕላን ከከተማው ማሪ ፕላን ጋር የማይቃረን መሆኑን እና የከሳሾች ይዞታ በካርታቸው ላይ ከሚያሳየው ኮርዲኔት አሁን ያለው የቤቱ ይዞታ ወደ መንገዱ ወጣ ብሎ የተቀመጠ መሆኑን በማጣራት ምላሽ ሰጥቷል። ፍ/ቤቱ በድጋሚ ባዘዘው ትዕዛዝ መሠረት

በኢትዮጵያ የኮንስትራክሽንና ዲዛይንና ሱፐርቪዥን የትራንስፖርት ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ዘርፍ በደብዳቤ ቁጥር ትዲቀስዘ/አጠ-ሀ3/221 በ21/01/2013 ዓ.ም በሰጠው ምላሽ የከሳሾች የይዞታ ካርታ የተሰጣቸው የመንገዱ ፕላን ከፀደቀ በኃላ መሆኑን፣የመንገዱ ፕላን የከሳሾችን ካርታ እንደማይነካ ነገር ግን ከሳሾች በካርታ ከያዙት ይዞታ ውጪ ወደ መንገዱ ወጣ ብሎ በአንዱ ጫፍ በ0.864ሜ እና በሌላ ጫፍ በ0.471 ሜ ወደ መንገድ እንደሚገባ በማጣራት ምላሽ ሰጥቷል፡፡ሙሉ ምላሹን ተጣሪቶ ከቀረበው ሰነድ እና ምስል መመልከት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ምላሾች የሚያሳዩት ከሳሾች ከተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ውጪ በአንዱ ጫፍ 0.864 ሜ እና በሌላ ጫፍ 0.471 ወደ መንገዱ እንደሚገባ በማጣራት ምላሽ ሰጥቷል፡፡

መሆኑም 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች መንገዱን ለመገንባት የተንቀሳቀሱት በከሳሾች ይዞታ ላይ ባለመሆኑ እና 2ኛ ተከሳሽ የመንገድ ፕላኑን የሰራው በከሳሾች ይዞታ ላይ ባለመሆኑ ተከሳሾች በከሳሾች ላይ የፈጠሩት የሁከት ተግባር የለም ተብሎ የቀረበውን የከሳሾችን ክስ ውድቅ በማድረግ ተወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

1. 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች መንገዱን ለመገንባት የተንቀሳቀሱት በከሳሾች ይዞታ ላይ ባለመሆኑ እና 2ኛ ተከሳሽም የመንገድ ፕላኑን የሰራው በከሳሾች ይዞታ ላይ ባለመሆኑ ተከሳሾች በከሳሾች ላይ የፈጠሩት የሁከት ተግባር የለም ተብሎ የቀረበውን የከሳሾችን ክስ ውድቅ በማድረግ ተወስኗል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ተከሳሾች ዝርዝሩን የማቅረብ መብት ተጠብቋል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1.ቅሬታ ላለው የይግባኝ መብት የተጠበቀ ነው።

2.በፍ/ቤቱ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል።

3.መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።